PANORAMA # 11

## የትዝብት አድማስ

ጥር 23 2000 ዓም ( ፌብርዋሪ 1 2008)

## በቀጣይነት መታገል የድል ዋስትና ነው

ለሕዝብ ነፃነትና ለሀገር ህልውና ሲሉ ተደራጅተው የሚታገሉ ኃይሎች፥ በየትኛውም ታሪክና ኅብረተስብ ውስጥ እንደነበሩና እንዳሉ የታወቀ ነው:: ይህ እርምጃ ጨቋኝና ተጨቋኝ እስካሉ ድረስ የሚቀጥል ክስተት ነው የሚሆነው:: አምባገነኖችን ለማስወገድም ይሁን ቅኝ ገዥዎችን ለማባረር ተደራጅቶ ትግል የጀመረው ሁሉ፥ እስከ መመጨረሻው የድል ቀን ድረስ መታገሉን ይቀጥልበታል፥ ማለት አይቻልም:: ምክንያቱም የጀመረው ሁሉ በአመነበት ዓላማው ፀንቶ እንዳልቀጠለ ያለፈው የትግል ታሪክ ብዙ ማስረጃ ስለሚነግረን ነው:: በኛው ሀገርም ቢሆን ለአለፉት ሠላሳ አራት ዓመቶች ትግል የጀመሩት ግለሰቦችም ይሁኑ ስብስቦች ሁሉ፥ በየወቅቱ እንደ እንጉዳይ የፈሉትን ያህል፥ በዚያው መጠንና ፍጥነት ከስመው እንደ ቀሩ ለመታዘብ ችለናል:: እንኳንስ በተለየዩ ድርጅቶች መካከል ይቅርና፤ በአንድ ድርጅት ውስጥ አብረው የጀመሩት ሁሉ በየትግሉ ምዕራፍ እየተንጠባጠቡ እንደቀሩ የታየ ሀቅ ነው:: ይህ በመሆኑ ደግሞ የሚያስገርም ሊሆን አይችልም:: በዓላማው የፀናው ይቀጥልበታል:: ያልፀናው ደግሞ ከትግሉ ሰልፍ ይወጣል:: ይህ ዓይነቱ ክስተት የነበረ፥ ያለና ወደፊትም የሚመጣ ነው:: ከትግሉ ሂደት በፍቃዳቸው የተወገዱ ሁሉ ሊነቀፉ የሚገባቸው አይመስለንም:: ችግሩ የሚመጣው ግን ትግሉን በዕምነታቸው ፀንተው የቀጠሉትን ኃይሎችም ሆነ፥ የታገሉበትን የድርጅት ምሥጢር ለጠላት አሳልፎ ለመስጠትና የሕዝቡን የትግል መንፈስ ለማኮላሸት ጥረት ሲደረግ ነው:: ይህ ጥረት በሚከሰትበት ጊዜ ኅብተረተሰቡም ሆነ ታጋዩ ኃይል ባርምሞ አይመለከትም:: ትግሉን ከጠላት ለመከላከል አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ይገደዳል::

በየትኛውም ኅብረተስብ ውስጥ አምባገነን ሥርዓት የሚያካሂው የጭቆና አገዛዝ ሲያንገፈግፈው፥ ማነኛውም ዜጋ በተለያዩ መንገዶች ተቃውሞውን መግለፁ የማይቀር ነው:: ሕዝባዊው ተቃውሞው፥ ቀስ በቀስ እየሰፋ፥ እየጎለመሰና እየተጠናከረ የሚሄድ ቢመስልም፥ቀጣይነት በሆነ መልኩ ሊራመድ ካልቻለ፥ ያመረቃ ውጤት ሊያስመዘግብ ይችላል ተብሎ አይጠበቅም:: በሥርዓቱ ላይ ዜጎች ተቃውሚቸውን የሚገልፁበት ምክንያቶች በርካታ ናቸው:: ከዕለታዊ የኑሮ ውድነት ጀምሮ፥ እስከ ከፍተኛ የፍትህ መጓደል፥ የሰብዓዊ መብቶች መጣስና የጅምላ ጭፍጨፋን ያጠቃልላል:: ጠቅለል ብሎ ሲነገር፥ የአንድ ሀገር ዜጎች፥በጨቋኝ ሥርዓት ላይ፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥

የማኅበራዊና የሰብዓዊ መብቶች መጣስ ጥያቄዎችን አንስተው ተቃውሟቸውን ለማሰማት ይገደዳሉ:: ጥያቄያቸው ቢቻል በሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ከተፈታላቸው፣ እሰየው ይባላል:: ያ ካልሆነ ደግሞ ልዩ ልዩ የትግል ስልቶችን በመጠቀም ጨቋኙን ሥርዓት ከማስወገድ የሚያግዳቸው ኃይል አይኖርም:: የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ደግሞ ዜጎች የማንንም ፈቀድ አያስፈልጋቸውም:: የአመጹ እንቅስቃሴ ምናልባት ከኅብረተሰቡ ግብታዊ ቁጣ ገንፍሎ ከወቅታዊው እንቅስቃሴ ባሻገር ሊያልፍ አይችልም ይሆናል:: ምክንያቱም የገዥው ክፍል በድንጋጤ በመርበርበትና በደመነፍሱ እየተወራጨ በታጠቀ ኃይል ለማዳፈን ስለሚችል ይሆናል:: ግን ደግሞ÷ ይህ ሕዝባዊ አመጽ በጊዜያዊ መልኩ የተዳፈነ ቢመስልም÷ የጭቆናው ክፋትና ክብደት በጨመረ ቁጥር እንደገና መቀስቀሱና ማገርሸቱ ብሎም ለትቂት ቀናት ብቻ ዕድሜ አግኝቶ የሥርዓቱን አራማጆች መልሶ ማርበትበቱ አይቀርም:: በዚህ አይነት ሁኔታ÷ በገዥና በተገዥ፣በጨቋኝና በተጨቋኝ ፍልሚያው መልኩንና ሂደቱን እየለዋወጠ ይቀጥላል:: ሥርዓቱ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ጭፍጨፋውን ሲቀጥልበት÷ ምልአተ ሕዝቡም በአልገዛም ባይነት ትግሉን ሲያፋፍመው÷ ቅረቀኔው ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይተላለፋል:: የአምባገነኑ የጭቆና መሳሪያ የሆኑት የሥርዓቱ የፀጥታና የአፈና ክፍሎች የሕዝቡን እንቅስቃሴ ለማዳፈን አረመኒያዊ ጭፍጨፋ ያካሂዳሉ:: የዚህ ዓይነት ግብ ግብ ልክ እንደ ሸማኔ መወርወሪያ ወዲያና ወዲህ እየተንከራተተ በጨቋኝና በተጨቋኝ መካከል ፍልሚያ አዙሪት ውስጥ ገብቶ ብቅ ጥልቅ እያለ ይሄዳል:: ይቆያል:: ለአለፉት 17 የመከራና የውርደት ዓመታት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጋር ያደረገው መስዋዕታዊ ትግልም ይህንን ሀቅ የሚያረጋግጥ ክስተት ነበር:: ይህ አዙሪት በማያዳግም መልኩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፍፃሜ የሚያገኝ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ዘረኛ ሥርዓት አስወግዶ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ሲገነባ ብቻ ነው:: በዕርግጥ ይህ ወቅት እስኪመጣ ድረስ÷ ሕዝባዊው ትግሉ በሁለንተናዊ መልኩ መቀጠል አስፈላጊም አንገብጋቢም ነው:: የትግሉ በሁለንተናዊ ገጽታው ወደ ተጨባጭ ውጤት ለመለወጥ ካስፈለገ÷ ትግሉ እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ብሎ በሚሰወር ሂደት ሳይሆን÷ ቀጣይነትና ዕድገት በሚያሳይ ሂደት እንዲራመድ ያስፈልጋል:: ለዚህ ሂደትም የማይናቅ ሚና ከሚጫወቱት የኅብረተስብ ክፍሎች መካከል÷ የሙያ ማኅበራት÷ የሴቶችና የወጣቶች ማኅበሮች÷ ነጋዴዎችና የሠራተኛው ክፍል÷ ጋዛጠኞችና የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ/ተቆርቋሪ÷ ምሁራንና ተማሪዎች÷ የመጓጓዣና የመገናኛ ተቋማት ሠራተኞች÷ ሀገር ወዳድ የፖሊስና የጦር መኮንኖች÷ ወታደሮች÷ የህክምና ሠራተኞችና ሐኪሞች÷ የሃይማኖት አባቶችና ተቋማት÷ በጠቅላላውም የገጠሩና የከተማ ነዋሪዎች እንደ አብነት የሚዘረዘሩ ናቸው:: ሁሉንም እያካተተ በተደረገ ብሔራዊ ትግል የሚመጣ ሕዝባዊ ድል÷ በዲሞክራሲ ግንባታ ላይ በሚመሠረተው የሀገር ዕድገትና ግንባታ የሚጫወተው ሚና ወሳኝነት አለው:: የትግሉንም ፍሬና አዝመራ ሁሉም በዕኩልነት ያገኛል:: ሁሉም የሀገሩን ዕድል-ፋንታ በጋራ የመወሰን ኃይልና ሥልጣን ይኖረዋል:: በሀገሪቱ ዕድገትና ልማት÷ ሥልጣኔና ዕርምጃ ሁሉም በጋራ ተካፋይ ይሆናል::አንድ ክፍል ወይም÷የተወሰኑ ወገኖች ብቻ በግል የድሉ አምጭዎች እኛ ነን ሊሉ አይችሉም::

ማንም ተገልሎ ሊቀር አይችልም። ይህም በመሆኑ ሰላምና መረጋጋት በዘለቄታ መልኩ የሚገኝበትን ሁኔታን ያመቻቻል ማለት ነው።
በዛሬው ጊዜ በሀገራችን ሰላምና ዕርቅ እንዲመጣ ካስፈለገ፥ በዕርግጥ የወያኔ መሪዎች ወደ ውይይት ጠረጴዛ ተገድደው ሊመጡ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር መቻል አለበት የሚሉ አሉ። ይህ ዕውን እንዲሆን የነመለስን የድንቁርና ትዕቢት የሚያስተነፍስ ወቅት ሊመጣ ይገባል ማለት ነው። አንድን የአምባገነን መንግሥት ለድርድር ወደ ክብ ጠረጴዛ እንዲመጣ ካስፈለገ፥ በዕርግጥ አስገዳጅ ሁኔታ እንዲመጣ የግድ ይላል። ለዚህ አስገዳጅ ሁኔታ ዓይነተኛ መሳሪያ፥ የተቀነባባረና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያከተተ አርዕድ አንቀጥቅጥ ሀገር አቀፍ ሕዝባዊ አመፅ ነው። ይህ ደግሞ በአንድ ቀን ዝምበር ቅስቀሳና አዋጅ የሚመጣ አይደለም። ብዙ ጥረትና የተራቀቀ ተግባርን የሚጠይቅ የትግል ስልት ነው። ለዚህ ሕዝባዊ አመፅና አድማ አጋዥ ከሚሆኑት ቅድመ ዝግጅቶች መካከል፥ የገዥው ፓርቲ አባላት ንብረት ከሆኑት የንግድና የፋይናንስ ተቋማት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አላማድረግ አንዱ ነው። በሁለንተናዊ መልኩ፥በስልት የተቀነባበረና ሁሉ-አቀፍ የኢኮኖሚክ ማዕቀብ ማድረግ፥ የአምባገነኑን ቅስም ሰባሪ የሆነ ተጽዕኖ ማድረግ ያስችላል። ይህ ሲደረግ፥ በአንድ ቀን ዝምበር ፈግኅ ወዲያው እንደሚረግፍ እንጉዳይ ብቅ ብሎ የሚጠፋ ሳይሆን፥ በቀናትና በሳምንታት ሊቆይ የሚችል ቀጣይና ግለት ያለው ተቃውሞ በማድረግ ነው። ይህ ትግል የአምባገነኖችን ቅስም ለመስበር የሚጫወት ሚና በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። በተለይም ስልት ባለው መንገድ ከተቀነባበረና የሁሉንምተሳትፎ ያካተተ ከሆነ፥ የገዥውን ፓርቲ ሥልጣን አርዕድ-አንቀጥቅጥ በሆነ መልኩ ያርበተብተዋል። ይዚህ ዓይነቱ ሕዝባዊ አመፅ የሰላማዊው ትግል ዋነኛ አካል ስለሚሆን ሥርዓቱን ተፃርሮ የቆመው የኅብረተሰብ ክፍል ሁሉ በአንድ ድምፅና በአንድ ልብ የሚሳተፍበት መሆን አለበት። እዚህ ላይ መጤን የሚገባው ይህ የትግል ሂደት ከገዥው ክፍል እክል የሚያጋጥመው መሆኑን ነው። አምባገነኖች ከሥልጣን ላለመልቀቅ ያለ የሌለውን ኃይል በመጠቀም፥ የሕዝቡን አመጽ ለማዳፈን በሚያደርጉት ጭፍጨፋ፥ የሰው ህይወት፥ የሀገር ንብረት፥ ይጠፋል ይወድማል። ከፍተኛ መሥዋዕት ይከፈላል። በግንቦት 97ም ያየነው ነው። ይህ ማለት ምን ማለት ነው? የሰላማዊ ትግል፥ ከትጥቅ ትግሉ ያልተናነሰ መራራ መሥዋዕትን ይጠይቃል ማለት ነው። ከመነሻው ይህንን ተገንዝቦ፥ ማነኛውንም ዓይነት መሥዋዕት ለመክፈል ሁለንተናዊ ዝግጅት ማድረግ፤ ትግሉን ከጥቃት ለመከላከል ብቻ ሳይሆን፥ ትግሉንም በቀጣይነት ለማራመድ የሚያስችሉ አዳዲስ ስልቶችን ለመንደፍ ያስችላል። ባለፈው ሁለት ዓመቱ የግንቦቱ አርዕድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመፅ፥ ያ ሁሉ የሰው ህይወት ጠፍቶ ሊከስም መብቃቱ፥ እንደ ማስረጃ ሊቆጠር የሚችል ክስተት ነበር። መለስና ግብረ-አበሮቹ ግን፥ የተዳፈነ እሳት የጠፋ መስሏቸው፥ በሕዝብ ላይ የሚያደርጉትን ግፍና በደል በአያሌው ቀጥለውበታል። ለዚህም ነው አገዛዙን በሁለገብ ትግል ማስወገድ የግድ የሚሆነው።

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ብቻ ሳይሆን፥ በጠቅላላው ምሥራቅ አፍሪካ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ ከአምባገነኖች ቁጥጥር ስር እየወጣ መሄዱ፥

*የቀጣይ ትግል ቀጥተኛ ውጤት ነው ለማለት ይቻላል። በብሔራዊ ምርጫ ውጤት የአምባገነኖች ውንብድናን አስመልክቶ፥ ከሁለት ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ የተደረገው ሕዝባዊ አመፅና በአሁኑ ወቅት በተመሳሳይ ክስተት በኬንያ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ የመነሻ ምክንያቱና ሂደቱ ተመሳሳይ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም። በሁለቱ ክስተቶች መካከል አንድ የማይካድ መሠረታዊ ልዩነት እንዳለ ግን ልንገነዘበው ይገባል። የእኛው ሕዝባዊ አመፅ ከአዲስ አበባ ውጭ በስፋትና በርዝመት ያልተቀጣጠለ በመሆኑ፥ ዕድሜው በአጭር ሲቀጭ፥ የናይሮቢው ግን መላውን ኬንያን እያጥለቀለቀ እስካሁን ቀጥሏል። ይህም የሚያሳየው፥ በቀጣይነት የሚደረግ ሕዝባዊ አመፅ ሁሉ ምን ያህል ልዩነት ሊያመጣ የሚችል መሆኑን ነው። ያለ መስዋዕትነት ነፃነት እንደማይመጣ ሁሉ፥ ስርዕየት ደግሞ በአንድ ሰላማዊ ሰልፍ ወይም በቅፅበታዊ ትግል ብቻ የሚያበቃ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ስርየት ሊያስገኝለት የሚችለው የራሱ ያልተቋረጠና ያልታከተ መስዋዕታዊ ትግል እንጅ፥ በሁለተኛ ደረጃ የሚፍጨረጨሩ የሌሎች የተቆራረጠና ያልተያያዘ ትግል አይደለም።
" ብልህ ከልባም ጉረቤቱ ጠቃሚ ትምህርትን ይቀስማል" የሚለውን ይትብኃል መገንዘብ ከተቻለ፥ ከአንድ ወር በላይ ትግሉን በማፋፋም ከፍተኛ መሥዋዕት ከሚከፈልበት ከኬንያ ሕዝብ ትግል ብዙ መማር የሚቻል ይመስለናል። ይህ ስለተባል ግን፥ ከውጭ የሚመጣውን ማነኛውንም ነገር ሁሉ እንዳለ አሰር ገሰሰሱን ሳያጣሩና ጠቃሚነቱን ሳያረጋግጡ መቀበል ማለት አይደለም። የወቅቱ የኬንያ ሕዝብ ትግል በቀጣይነቱና በሚከፈለውም መሥዋዕት ሊደነቅ ቢችልም፥ አመፁ አቅጣጫውን በመሳት ወደ ጎሳና ወደ ሕዝብ የእርስ በእርስ ዕልቂት ማምራቱ የሚደገፍ ሊሆን አይችልም። የወያኔ መሪዎች የሕዝቡን ሀገር አቀፍ የትግል አመፅ ወደ ጎሳ የእርስ በዕርስ ፍጅትና ዕሊቂት እንዲያመራ ያደረጉት እኩይ ጥረት ሁሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይነት በተደጋጋሚ የከሸፈ መሆኑን ብንረዳም፥ ይህን በኬንያ የተከሰተውን አደገኛ አዝማሚያ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአርምሞ የሚያየው ብቻ ሳይሆን፥ በጥንቃቄ ሊመለከተው የሚገባ ነው ማለት ይቻላል። በአደገኛ የክፍፍል ፖለቲካ የሚጫወተውም የወያኔ አገዛዝ ውሉ ከተፈታ ምን ሊመጣ እንደሚችልና ማንስ ተጎጂ ሆኖ እንደሚጋለጥ ትምህርት ሊቀስምበት ቢችል መልካም ይሆናል። ቀኝም ነፈሰ ግራ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ትግል፥ ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ፥ ያልተቋረጠ ትግል ማካሄድ ወሳኝ ነው። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ተቃዋሚ ድርጅቶች ዘረኛውን ሥርዓት በማንበርከክ ደረጃ ጠንካራ ሆነው መውጣትን ይጠይቃል።*

---------------------- /////////////----------------------